<u>ሐዋርያዊ መልሶች - Apostolic Answers</u>

<u>ተከታታይ የክርስትና ትምህርት መስጫ አጋዥ ጽሑፍ - 3</u>

# <u>እውነተኛው አምላክ የክርስቲያኖች አምላክ እንደሆነ በምን እናውቃለን..??</u>

## <u>የኢየሱስ ትንሳኤ፡</u>

ትልልቅ የሚባሉ ቤተ እምነቶች ሁሉ ስለ ኢየሱስ የሚሉት የሆነ ነገር አላቸው.. አንዳንዶች አንድ መምህር ነው ሲሉ ሌሎች ነቢይ ይላሉ.. የእርሱ ተከታዮች ደግሞ ሥጋ ሆኖ የመጣ አካላዊ የእግዚአብሔር ቃል ወይም ልጅ ነው እንላለን። ይህም ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ እንደ ሞተ እና ደግሞም እንደ ተነሣ እናምናለን። የጌታችን መነሣት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። ምክንያቱም ብዙዎች ትንሳኤ ሙታን እንኳን የለም ይላሉና። ጌታ ግን እነሳለሁ አለ የምርም ተነሣ.. እኛም ደግሞ ሞተን እንደማንቀር ነገረን.. ስለዚህም በኢየሱስ ሕይወት አለ። ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንኖራለን። ይህ ትልቅ ተስፋ ነው። ተስፋውም እንዲሁ የመጣ ሳይሆን ኢየሱስ የትንሳኤያችን በኩር ሆኖ ከሙታን ስለተነሣ ነው። ስለዚህም የኢየሱስ ትንሳኤ በክርስትና ውስጥ እንደ ማእከልም ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡ "ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት"[1ቆሮ 15፡14]

ጌታችን ኢየሱስ የእውነትም ከተነሳ የሐዋርያት ስብከት ከንቱ አትሆንም.. ስለዚህም ክርስትና እውነት ይሆናል። ታድያ ግን ክርስቶስ ካልተነሣ ስብከታቸው ሁሉ እንዲሁ ከንቱ ነው.. ክርስትናም ሐሰት ይሆናል። ለምሳሌ አንድ ሙስሊም እስልምናው ትክክል መሆን አለመሆኑን በእርግጠኝነት ሊያውቅ የሚችለው እርሱ ራሱ ግለሰቡ ሲሞትና ሄዶ ሲያረጋግጥ ነው። ምክንያቱም ወይ ነቢዩን ሙሃመድን አግኝቶት አያውቅ "ነቢዩ" ራሱም እውነተኛ ለመሆኑ ሞቶ እንደማይቀርም ምንም ማስረጃ ከቃል የዘለለ ማስረጃ ስለማያስቀምጥ። ክርስትና ላይ ግን ኢየሱስ ሞቶ እንዳልቀረ እንደ ተነሣ ሐዋርያቱ አይተዋል መስክረዋልም.. ስለዚህም ኢየሱስ ሞቶ እንደማይቀር እንደሚነሳ የገባውን ቃል ከፈጸመ እንዲሁ ደግሞ እኛም ሞተን እንደማንቀር የሰጠንን የተስፋ ቃል እንደሚፈጽመው በተስፋ እንቀበለዋለን። እውን ግን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ተነስቷል..?? ለምሳሌ እስልምና ኢየሱስ ተነስቷል የሚለውን ብቻ ሳይሆን ተሰቅሏል የሚለውንም ጭምር ይክዳል። ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማሳየቱ በእጅጉ ቀላል ነው.. ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ትምህርቱም እርሱ ስለሆነ። ታድያ ግን መጽሐፍ ቅዱስን አልቀበልም ሐዋርያቱ ዋሽተዋል ለሚልስ ሰው..??

ተነስቷል..?? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከመነሣት በፊት የሚቀድሙ ነገሮችን እናንሳ.. የምርም ሲጀመርስ ተሠቅሏል..?? ከመሠቀልም ደግሞ መወለድ ይቀድማልና የምርም ኢየሱስ የሚባል አካል በታሪክ ውስጥ ይታወቃል..?? ለምሳሌ አንዳንዶች ሙሐመድ የሚባል ነቢይ በታሪክ ውስጥ አይታወቅም በእስላማዊ መጽሐፍት ውስጥ ካልሆነ በስተቀር የሚሉ አሉ.. ኢየሱስስ..??

## እውን ኢየሱስ የሚባል ሰው በታሪክ ውስጥ ነበር..??

ጌታችን ኢየሱስ እንዳልኳችሁ ራሱን እስልምናን ጨምሮ በሌሎች ትልልቅ የሚባሉ ቤተ እምነቶች ሳይቀር የሆነ የሚባልለት ነገር አለ።

ለምሳሌ በአይሁዳውያን ዘንድ ኢየሱስ **አስተማሪ** እንደነበር እና የተወሰኑ ደቀመዛሙርት እንደነበሩት እና **አስማት**(sorcery) **አድርጎ** እስራኤልን አስሳተ ብሎ የሚወቅስ ባህል ከ3ኛው እስከ 6ኛው ክ/ዘመን በተዘጋጀው በታልሙዳቸው ውስጥ ተከትቦ አለ [ለምሳሌ sanhedrin 43a : https://www.sefaria.org/Sanhedrin.43a.20?lang=bi ] ከዚህ አንድ ልንይዝ የምንችለው ነገር ጌታ እንደነበረ ብቻ ሳይሆን መምህርም እንደ ነበር እና ደግሞ ተአምር አድራጊም ጭምር እንደ ነበር ነው። ያው ጌታ በሥጋው ወራት ተአምራትን ሲያደርግ ፈሪሳውያኑ ግን "ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን

አያወጣም”[ማቴ 12፡ 24] ሲሉ እንደ ነበሩት ሁሉ በኋላ የተነሱ የአይሁድ ሊቃውንትም ተአምሩ ከአጋንንት አለቃ እንደሆነ ለመናገር ደፍረዋል። ታድያ ግን እንዳትረሱ ከእርዚህ የምንወስደው አንድ ነገር ጌታ እንደ ነበርና ተአምራትንም ያደርግ እንደ ነበር ከራሳቸው ከአይሁዳውያን ሳይቀር ማስረጃ ማግኘታችንን ነው።

ወደ ሂንዱይዝም እና ቡዲዝም ስትሄዱ ደግሞ ብዙ ተከታዮቻቸው ኢየሱስን እንደ ቅዱስ ታላቅ መምህር የሚመለከቱት አሉ። እስልምና ደግሞ ብዙዎች እንደምናውቀው የፈጣሪ ነቢይ ተአምር አድራጊ እና መሰል ነገሮችን ሰጥቶት እንመለከታለን(ያው በቁርአን ሳይቀር ማለት ነው) ከቤተ እምነቶች አንጻር አንስቼ ያሳየኋችሁ ቢያንስ ብዙዎች ኢየሱስ እንደሚሉ ለማሳየት እና ተጽእኖውን ለማሳየት ነው። ይህንን እያየን ኢየሱስ የሚባል አካል ጭራሹኑ አልነበረም ለማለት ያስቸግራል።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ጥሩ የታሪክ ማስረጃም ማቅረብ እንችላለን። ባርት ኤርማን የተባለ አግኖስቲክ የመጽሐፍ ቅዱስ(ማለትም ከጽሑፋዊ ነገርነቱ አንጻር ብቻ) ምሁር የሆነ ሰው በዚሁ ርዕስ ላይ ማለትም “እውን ኢየሱስ የሚባል ሰው ነበርን..??” በሚለው ላይ መጽሐፍን ጽፏል። የመጽሐፉም ስም “Did Jesus Exist? The Historical Argument for Jesus of Nazareth” ይሰኛል። በዚህም መጽሐፉ የመግቢያ ክፍሉ ላይም እንደሚያሳውቀው የክርስትናን አጀንዳ የማስተዋወቅ የተለየ ፍላጎት የሌለው ወደ ኤቲስት ያጋደለ አግኖስቲክ የሆነው ባርት ኤርማን እንዲህ ይላል፡ “ስለ ኢየሱስ በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ እይታዎች ቢሰጡም በምድራችን ላይ ያሉ የዘርፉ ምሁራን ሁሉ ግን ስለ ኢየሱስ ከሚስማሙባቸው ነገሮች ውስጥ ኢየሱስ እርሱ አይሁዳዊ ሰው እንደ ነበር እና መምህርና አስተማሪ የነበረ ሰው ጲላጦስ የይሁዳ ገዢ በነበረበት ጊዜም በኢየሩሳሌም እንደ ተሠቀለ ነው”[idib, Evidence for the Historical Jesus: chap 1] በመጽሐፉ ላይ የተለያዩ ማስረጃዎችን በማቅረብ የኢየሱስንም መኖር(exist እንደ ሚያደርግ) ይሞግታል። ጥንታዊ ከሚባሉ ታሪካዊ ማስረጃዎች ሁለቱን እንጥቀስ፡

የመጀመሪያው ጆሴፈስ የተባለው አይሁዳዊ የታሪክ ምሁር(historian) ነው.. ጆሴፈስ ለክርስቶስ ታሪክ እጅጉን ቅርብ የነበረ ሰው ነው። በ1ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ የነበረ አይሁዳዊ ሰው እንደ ሆነ ይነገርለታል። ይህ ሰው ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ተቀብሎ ወደ ክርስትና አልመጣም። ታድያ ግን ስለ እርሱ ማለትም ስለ ኢየሱስ ሲናገር ኢየሱስ ታላቅ መምህር እና ተአምራትን ያደርግ የነበር ሰው እንደ ነበረና በኋላም በጴንጤናዊው ጲላጦስ በመስቀል የተፈረደበት እንደሆነ ይናገራል [Antiquities of the Jews, 18:3:3]።

ሁለተኛው ደግሞ ታሲተስ(Tacitus) ነው.. ታሲተስ ሮማዊ ነው.. እና 1ኛው ክ/ዘመን ላይ የነበረውን የሮማውያንን ታሪክ ያስተላለፈ ሰው ነው። እና ብዙ ተአማኒነት ያለው ሁነኛ ማስረጃ ነው ማለት ይቻላል.. እና ይህ ሰውም ክርስቲያኖች ስማቸውን ከየት እንዳገኙ ሲናገር በጴንጤናዊው ጲላጦስ ሞት በተፈረደበት በክርስቶስ ክርስቲያን እንደ ተባሉ ይናገራል [Annals, 15፡ 44] እንግዲህ እጅግ ጥንታውያን የሚባሉ ለክርስቶስ ታሪክ በእጅጉ የቀረቡ ከክርስትና ውጪ የሆኑ አይሁዳዊና ሮማዊ ታሪኮችም እንደሚያሳዩን ኢየሱስ የሚባል አካል የምርም እንደ ነበር ብቻ ሳይሆን እንደ ተሰቀለም ጭምር ነው።

ከዚህ ውጪ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስንም እንደ ታሪክ መጽሐፍ ልንጠቅሰው እንችላለን ለኢአማንያን።

መልካም ኢየሱስ እንደ ነበረና እንደ ተሰቀለም አወቅን። ትንሣኤውስ..??

## <u>ለኢየሱስ ትንሳኤ ማስረጃ</u>

ኢየሱስ እንደ ተነሣ አራቱም ወንጌላት እንዲሁም ጳውሎስም በስፋት ዘግበውታል። ጌታ መሞቱን ሁሉም ቢያምንም ታድያ ግን ትንሳኤውን ይክዳሉ። የጌታን ትንሣኤ ለማስረዳት ልናስታውስ የሚገባው ነገር ሐዋርያቱ በኢየሩሳሌ የጌታችንን ትንሣኤ ሰበኩ። ሞቶ እንዳልቀረ ስለዚህም መቃብሩ ባዶ እንደ ሆነ ሰበኩ። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ቀን ቅዱስ ጴጥሮስ ወጥቶ ሰበከ ሲሰብክም የጌታችንን ትንሣኤ በግልጽ አወጀ ለዛም ምስክሮች እንደሆኑ ተናገረ[ሐዋ 2፡31-32] በዚህም ደግሞ ልባቸው ተነክቶ ሦስት ሺህ ነፍሳት ከአይሁድ ወደ ክርስትና መጡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጨመሩ። እዚህ ላይ አንድ ነገር እንጠይቃለን.. ሐዋርያቱ በግልጽ በኢየሩሳሌም የኢየሱስን ትንሣኤ በመስበክ መቃብሩ ባዶ እንደሆነ ሲያውጁ በእርዚህም ደግሞ ብዙዎች የአይሁድ እምነትን ሲተዉ ፈሪሳውያኑ ሲያዩ የሐዋርያቱ የትንሣኤው ትምህርት ስህተት ከሆነ ሊያደርጉ የሚችሉት አንድ ነገር አለ.. ይህም ወደ መቃብሩ ሄዶ መቃብሩ ባዶ እንዳልሆነ ማሳየት። ግን ሊያደርጉት አልቻሉም። ምክንያቱም መቃብሩ የምርም ባዶ ነበር። ስለዛ ያላቸው አማራጭ ከመቃብር ሰርቀው ወስደውት ነው የሚል ነው። ይህ በወንጌልም ተዘግቧል። የመቃብሩ ጠባቂዎች ወደ ከተማ ገብተው ለካህናት አለቆች እንደተናገሩና የካህናት አለቆችም ከሽማግሌዎቹ ጋር ተሰብስበው “እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ” ብለው ለጠባቂዎች ይመክሯቸዋል[ማቴ 28፡ 11-15]

እውን ግን ሥርቀውት ይሆን..?? ሊሆን አይችልም ምክንያቱም አንደኛ ሲሰቀል ጥለው የሸሹ ከተቀበረ በኋላ ደግሞ ያውም ጠባቂ እያለ ሊሰርቁ የሚሄዱበት ድፍረት የሚኖራቸው አይመስለኝም። በዛ ላይ ደግሞ ሰርቀው ምን ሊጠቀሙ..?? ምክንያቱም ሰረቁ ብንል ራሱ እንኳን ከሰረቁት በኋላ ኢየሱስ ተነሣ ብለው ሰብከዋል ይህ ደግሞ ያመጣባቸው መገደል ነው። ያልተፈጠረ ነገር ተፈጥሯል እያለ ራሱን አሳልፎ ማን ይሰጣል..?? ለምሳሌ ይላል አንድ ካቶሊክ ዐቃቤ እምነት አንድ ሙስሊም አጥፍቶ ጠፊ ቢሆንና ራሱን አጥፍቶ ሌላውንም ቢያጠፋ ይህንን የሚያደርገው ምናልባት እንደው ፈጣሪ በጀነት ይሸልመኛል ብሎ በማመን ነው። እና እውነተኛ ይሁን አይሁን እምነቱም አያውቅም በእርግጥም ያው ያየው ነገር የለምና። ቢሆንም ግን እንደው ራሱንም ሌላውንም የሚያጠፋው የወደፊቱን እያሰበ ነው። ሐዋርያቱ ግን ራሳቸው ሰርቀውት ከሆነ ጭራሽ የእግዚአብሔርንም መንግስት አያስቡም ያውም ኢየሱስ ካልተነሣ "ስብከታችን ከንቱ ናት" ብለዋል። ታድያ ዋሽተው መገደላቸው ስለምን..?? ስለዚህም ሰርቀውት እንዲሁ እየዋሹ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

አንዳንዶች ደግሞ ሐዋርያቱ አዎ ኢየሱስን ከሞተ በኋላ አይተውታል ይላሉ.. ግን ደግሞ ካዩት አሰቃቂ ነገር አንጻር እንደው ቅዠት(hallucination) ዓይነት ነገር ነው ይላሉ። መታየቱን አሳማኝ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ የጳውሎስ ወደ ክርስትና መመለስ ነው። ምክንያቱም እርሱም እንዳየው ተናግሯል። እርሱም ብቻ አይደለም በ1ቆሮ 15 ላይ እንደሚያስቀምጠው ከ500 ለሚበዙ ወንድሞችም እንዲሁ ጌታ ታይቷል። ታድያ ግን በቅዠት መልክ ቢታይስ..?? በቅዠት መልክ ቢታይ የሚታየው በግል እንጂ በማሕበር አይታይም። ሲቀጥል ቅዠት ከሆነ ቀላል መንገድ ሄዶ መቃብሩን ቼክ ማድረግ ነው። መቃብሩ ደግሞ ባዶ ነው።

ሌላው ወንጌል ላይ እንደ ተገለጸው የኢየሱስን ትንሣኤ አስቀድመው የመሰከሩት ሴቶች ናቸው። በዛን ወቅት ሴቶች ተአማኒነት የላቸውም። እና ወንጌሉ ላይ ጸሐፍቱ(የወንጌል ጸሐፍያን) እንዲሁ እየዋሹ ቢሆን ተአማኒነት እንዲኖረው እነ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወይም ወንዶችን ባደረጉ ነበር። ነገር ግን ያለው እውነታ የሴቶቹ ስለሆነ ራሱኑ ጽፈውታል።

ማጠቃለያ፡

ጌታችን ተነሥቷል.. ቃሉንም ጠብቋል። ስለዚህም ለእኛም የገባልንን ቃሉ ሁሉ ይጠብቃል ብለን እናምናለን። በእርሱ በኩል የተገለጠውም አምላክ እውነተኛው አምላክ እንረዳለን።